አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like the River

ቁጥር 17, ሚያዚያ 2013 ዓ.ም. | Issue No. 17, April 2021

# አዋሽ ዜና መጽሔት
# Awash Newsletter

በማርኬቲንግና ኮምዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት የሚታተም
Published by Marketing & Communication Directorate

ልዩ የተማሪዎች የቁጠባ ሂሳብ

# Student

## Saving Account

" ዛሬን ለነገ "



አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like the River

ዋና አዘጋጅ: ተሾመ ዋቅጅራ
ረዳት አዘጋጆች: ሰላም ተክለጽዮን
ድሪባ መገርሳ
ፎቶግራፍ: ዳንኤል ምትኩ

EDITOR-IN-CHIEF: Teshome Wakjera
ASSISTANT EDITORS: Selam Tekletsion
Deriba Megerssa
PHOTOGRAPHER: Daniel Mitiku

# በዚህ እትም


የአዋሽ ባንክ አ.ኤ.አ. የ2020/21 የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት
የስራ አፈፃጸም ግምገማ ተካሄደ ......1

አዋሽ ባንክ ከመቶ ምርጥ የአፍሪካ ባንኮች ተርታ መሰለፍ ቻለ ......3

በልዩ የቁጠባ ሂሳቦች የተሰበሰበው ተቀማጭ ገንዘብ አበረታች መሆኑ ተጠቆመ ......4

አዋሽ ባንክ ከካናዳ ክርስቲያን ህፃናት ፈንድ ከተሰኘ
ግብረ ሰናይ ድርጅት ጋር በመተባበር የመማሪያ ክፍሎችን አስገነባ ......5

አዋሽ ባንክ ከኢትዮጵያ የወንጌል አማኞች አቢያተ ክርስቲያናት
ካውንስል ጋር የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረመ ......6

አዋሽ ባንክ የአርሶ አደሮችን የቁጠባ ባህል በማሳደግ ላይ እየሰራ ነው ......7

አዋሽ ባንክ ባመቻቸው ብድር የዳንግላ ከተማ ዙሪያ
አርሶ አደሮች ተጠቃሚ ሆኑ ......7

አዋሽ ባንክ ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት ጋር በመተባበር በመጋዘን
ደረሰኝ መያዣነት የብድር አገልግሎት መስጠት ጀመረ ......8

አዋሽ ባንክ ለገንዘብ ቁጠባና ብድር ማህበራት አማራጭ
የፋይናንስ አገልግሎቶችን አቀረበ ......9



8980
12638
www.awashbank.com
contactcenter@awashbank.com
SWIFT Code: AWINETAA


# IN THIS ISSUE


Digital Banking Technology ...... 11
Five Financial Goals you should have for 2021 ...... 13
Photo Reel ...... 14
Proverbs & Quotes ...... 19


አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like the River

# የአዋሽ ባንክ አ.ኤ.አ. የ2020/21
## የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት የስራ አፈፃፀም ግምገማ ተካሄደ




የአዋሽ ባንክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ፀሐይ ሽፈራው በጉባኤው ላይ የመክፈቻ ንግግር ሲያደርጉ

የአዋሽ ባንክ አ.ኤ.አ. የ2020/21 የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት የስራ አፈፃፀም ግምገማ የካቲት 20 እና የካቲት 27 ቀን 2013 ዓ.ም በአዲስ አበባ ኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል ተካሂዷል፡፡

በጉባኤው ላይ የባንኩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ፀሐይ ሽፈራው የግማሽ መንፈቅ ዓመቱን የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ያቀረቡ ሲሆን በዋና ዋና የሥራ አፈፃጸሞች ላይ ያተኮሩ ማብራሪያዎችን ሠጥተዋል። በዚህም መሰረት፡-

የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ በሀገራችን የተከሰተበትን ወቅት በማስታወስ እንዲሁም በኢኮኖሚው ላይ ያሳደረውን አሉታዊ ተጽዕኖ በማንሳት ያብራሩ ሲሆን ወረርሽኙን በመቋቋም የባንኩ ሠራተኞች ደህንነታቸው ተጠብቆ የተሻለ የሥራ አፈጻጸም ለማምጣት በባንኩ የተደረጉ የተለያዩ ጥረቶችና የተወሰዱ እርምጃዎችን በዝርዝር አስረድተዋል፣

በ2020/21 የመጀመያው ግማሽ ዓመት ከተከናወኑ ሥራዎች መካከል በዋናነት ከብር ኖት ቅያሪው ጋር ተያይዞ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ መሰረት የአዲሶቹ የብር ኖቶች ቅያሪ እንደተጀመረ በአዲስ አበባ እና በተመረጡ የተለያዩ የክልል ከተሞች አገልግሎቱን በፍጥነት በማዳረስ የመጀመርያው የግል ባንክ ከመሆኑም ባሻገር ከኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የተረከባቸውን የብር ኖቶች ለሌሎች ባንኮች በማሰራጨት ረገድ ሀገራዊ ግዴታውን ለመወጣት መቻሉን ጠቁመዋል፣

የባንኩ ባለአክስዮኖች 25ኛው መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ በተያዘለት መርሃ-ግብር መሰረት መካሄዱን አስታውሰው በጉባኤውም ላይ በርካታ ውሳኔዎች መተላለፋቸውን ገልጸዋል።

የባንኩ ተቋማዊ አደረጃጀት (Organization Structure) ለባንኩ ተከታታይ እድገትና ውጤታማነት ሲባል በአዲስ መልክ መደራጀቱን፣ የባንኩን አገልግሎት በይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ በተደረገው እንቅስቃሴ የበጀት ዓመት የመጀመሪያ አጋማሽ ብቻ 42 አዳዲስ ቅርንጫፎች ተከፍተው ለአገልግሎት መብቃታቸውን አስረድተዋል።

በሌላ በኩል በውጭ አማካሪ ድርጅት ተጀምሮ ሳይጠናቀቅ በመሃል የተቋረጠው የባንኩ Performance Management System (PMS) በግዜያዊነት በባንኩ ሠራተኞች ተዘጋጅቶ በዋ/መቤትና በሁሉም ቅርንጫፎች ተግባር ላይ እንዲውል መደረጉንና ይህም ሰራተኞችን በስራቸው በመመዘን ለማበረታታትና ለማሳደግ የሚያስችል መሆኑን አስረድተዋል።

ከባንኩ የፋይናንስ አፈፃጸም አንጻር እ.ኤ.አ ዲሴምበር 2020 መጨረሻ ላይ የባንካችን ጠቅላላ የተቀማጭ ሂሳብ 87.1 ቢሊዮን የነበረ ሲሆን ይህም አሃዝ ከተቀመጠው እቅድ አንጻር የብር 3.5 በመቶ ቅናሽ ማሳየቱንና ለዚህም ብቸኛው ምክንያት የቁጠባ ሂሳብ አሰባሰባችን ላይ የሚታዩ ክፍተቶች መሆናቸውን ጠቁመው የተሻለ ውጤት ማምጣት እንዲቻል ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መስራት እንደሚያስፈልግ አስገንዝበዋል።




የጉባኤው ተሳታፊዎች በከፊል

ባንኩ ለተለያዩ ክፍለ ኢኮኖሚዎች የሰጠው ብድር ከእቅድ በላይ የአምስት በመቶ አፈጻጸም ያስመዘገበ ሲሆን የባንኩ ጠቅላላ ገቢ ከባለፈው አመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር ብር 6.2 ቢሊዮን መድረሱንና የባንካችን ጠቅላላ ወጪ ደግሞ ብር 3.9 ሚሊዮን መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ለባንኩ ወጪ መጨመር የሠራተኞች ደመዎዝና ጥቅማ ጥቅም መሻሻል አንዱና ዋነኛው ምክንያት ነው ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚው በሠራተኛው ውጤታማነት ላይ አተኩሮ መስራት አስፈላጊ መሆኑን አስምረውበታል።

የባንኩ ያልተጣራ ትርፍ እ.ኤ.አ ዲሴምበር 2020 መጨረሻ ላይ 2.2 ቢሊዮን መድረሱን በመግለጽ ባጠቃላይ በመንፈቅ አመቱ የተገኙት ውጤቶች ተስፋ ሰጪና እጅግ የሚያበረታታ ቢሆንም ካስቀመጥነው ግብ አኳያ እንዲሁም ከሚገጥመን ብርቱ ፉክክር አንጻር ገና ብዙ መስራት እንደሚገባም አሳስበዋል። በዚህም መሰረት በተቀሩት የሂሳብ ዓመቱ ግዜያት ለስራ የሚያስፈልጉ የሰራተኞች ምደባ፣ የቢሮና የዕቃ አቅርቦት መሟላት በአዲሱ አደረጃጀት መሰረት ሁሉም የስራ ክፍሎች የተጣለባቸውን ሃላፊነትና ግዴታ መወጣት እንደሚገባ፣ በተቀማጭ ሂሳብ ማሰባሰብ እንዲሁም በውጭ ምንዛሬ ግኝት ረገድ ሰፊ ስራዎችን መስራት እንደሚገባ፣ የዲጂታል ፋይናንሺያል ሰርቪስ ላይ ብርቱ ጥረት ማድረግ እንደሚያስፈልግ እንዲሁም የደንበኞችን አገልግሎት ይበልጥ ለማሻሻል ምቹና ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በስራ ላይ ለማዋል ጥረት እንደሚደረግ ባስቀመጡት የትኩረት አቅጣጫዎች ውስጥ አካተዋል።

# አዋሽ ባንክ ከመቶ ምርጥ
## የአፍሪካ ባንኮች ተርታ መሰለፍ ቻለ

አዋሽ ባንክ በተጠናቀቀው የአውሮፓውያን 2020 ሂሳብ አመት አፍሪካ ውስጥ ከሚገኙ 100 ምርጥ ባንኮች መካከል የ90ኛ፣ ከምስራቅ አፍሪካ ደግሞ 14ኛ ደረጃ በመያዝ ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ የግል ባንኮች መካከል ቀዳሚነቱን በመያዝ አመቱን ማጠናቀቁን አፍሪካ ቢዝነስ እና ዘ አፍሪካ ሪፖርት አመላክተዋል፡፡

በሪፖርቱ እንደ ተመለከተው አዋሽ ባንክ ከሁለቱ የመንግስት ባንኮች ማለትም ኢትዮጵያ ንግድ ባንክና ልማት ባንክ ቀጥሎ ከአፍሪካ መቶ ምርጥ ባንኮች ተርታ ሊገባ የቻለ ብቸኛው የኢትዮጵያ የግል ባንክ ነው፡፡

ባንኩ ይህንን ደረጃ ሊያገኝ የቻለው 249 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ካፒታል፣ 2.6 ቢሊዮን አሜሪካ ዶላር ጠቅላላ የሀብት መጠንና 84 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ትርፍ በማስመዝገብ መሆኑን ሪፖርቱ አብራርቷል፡፡

አዋሽ ባንክ እ.ኤ.አ. በ2025 ከምስራቅ አፍሪካ ምርጥ አስር ባንኮች አንዱ የመሆን ራዕይ ሰንቆ ባዘጋጀው ፍኖተ ካርታ መሰረት በእያንዳንዱ የሴክተሩ ዕድገት መለኪያዎች በየዓመቱ እያስመዘገበ በመጣው አበረታች ውጤት በተጠናቀቀው የፈረንጆች ዓመት ከክፉለ አህጉሩም 14ኛ ደረጃ ላይ ሊደርስ ችሏል፡፡

ይህም ባንኩ በየደረጃው ያሉትን አመራሮቹንና ሰራተኞቹን በማስተባበር የአገልግሎት አሰጣጡን ከጊዜው ጋር እያዘመነ በመሄድ፣ የደንበኞችን እርካታ እያረጋገጠ እንዲሁም ተመራጭነቱን እያስመሰከረ ከሄደ የ2025 ራዕዩን እውን እንደሚያደርግ አመላካች ነው፡፡

# በልዩ የቁጠባ ሂሳቦች የተሰበሰበው
# ተቀማጭ ገንዘብ አበረታች መሆኑ ተጠቆመ

በባንካችን ተግበራዊ በተደረጉ ልዩ የቁጠባ ሂሳቦች እ.ኤ.አ. እስከ መጋቢት መጨረሻ 2021 ድረስ የተሰበሰበው ተቀማጭ ገንዘብ አበረታች መሆኑን በበጀት ዓመቱ ሶስተኛ ሩብ ዓመት መጨረሻ ላይ በተደረገው የቅርንጫፎች ጉብኝት እና ከሪፖርቶች መረጋገጡ ተገለፀ፡፡

በስራ ላይ በዋሉት ልዩ የቁጠባ ሂሳቦች የተሰበሰበው ተቀማጭ ገንዘብ እ.ኤ.አ. በሰኔ መጨረሻ ላይ 2020 ከነበረበት ብር 2.85 ቢሊዮን እ.ኤ.አ. መጋቢት 31/ 2021 ላይ የብር 3.57 ቢሊዮን ጭማሪ በማሳየት ብር 6.42 ቢሊዮን ደርሷል፤ ይህም 147 በመቶ ጭማሪ ማሳየቱን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ይህንን ተቀማጭ ገንዘብ ለመሰብሰብ የደንበኞች ወይንም የቆጣቢዎች ቁጥር ከፍተኛ ሚና እንዳለው ይታወቃል። ስለሆነም አዳዲስ የልዩ ቁጠባ ሂሳብ ተጠቃሚ ደንበኞችን ለማፍራት በተደረገው እንቅስቃሴ የቆጣቢዎች ብዛት 569,032 የደረሰ ሲሆን የደንበኞች ቁጥርም በመጋቢት ወር ብቻ በ52,704 ጨምሯል፡፡ በልዩ የቁጠባ ሂሳቦች ተቀማጭ ገንዘብ ለመሰብሰብ የታቀደውን ዕቅድ ሁሉም ሪጅኖች ያሳኩ ሲሆን አዳዲስ ደንበኞችን ከማፍራት አኳያ የተቀመጠውን ግብም ከሰሜን ሪጅን በስተቀር ሁሉም ማሳካታቸውንም በሪፖርቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በወርሃ መጋቢት ከልዩ ቁጠባ ሂሳብ ብር 129 ሚሊዮን በመሰብሰብ ከአዲስ አበባ ቅርንጫፎች የምስራቅ አዲስ አበባ ሪጅን ቀዳሚውን ስፍራ ሲይዝ፣ ብር 24 ሚሊዮን በመሰብሰብ የሰሜን ምዕራብ ሪጅን በክልሎች ከሚገኙ ቅርንጫፎች በሁለተኛነት ይከተለዋል፡፡ በሌላ መልኩ አዳዲስ የልዩ ቁጠባ ሂሳብ ተጠቃሚ ደንበኞችን ከማፍራት አኳያ 9,765 አዳዲስ ደንበኞችን በማፍራት የደቡብ አዲስ አበባ ሪጅን በአንደኝነት ደረጃ ሲመራ 7,553 አዳዲስ ደንበኞችን በማፍራት አዳማ ሪጅን በሁለተኝነት ደረጃ ይከተለዋል፡፡

ምንም እንኳን በልዩ የቁጠባ ሂሳቦች አዳዲስ ደንበኞችን የማፍራትና ተቀማጭ ገንዘብን ከመሰብሰብ አኳያ በመጋቢት ወር የተሰራው ስራና የተገኘው ውጤት አበረታች ቢሆንም ይህ የተመዘገበው ውጤት በተወሰኑ ፕሮዳክቶችና ቅርንጫፎች ላይ ብቻ መሆኑ ግን ለጉዳዩ ልዩ ትኩረት መስጠት የሚሻ መሆኑን ያሳያል፡፡ ለአብነትም ከተሰበሰበው ተቀማጭ ገንዘብ 50 በመቶ የሚሆነው ከሉሲ የሴቶች ልዩ የቁጠባ ሂሳብ ሲሆን፣ ከተሰበሰበው አጠቃላይ ተቀማጭ ገንዘብ ውስጥ 85 በመቶ የሚሆነው ከሉሲ የሴቶች ልዩ የቁጠባ ሂሳብ፣ ከአዋቂዎች ልዩ የቁጠባ ሂሳብ እና ከሳለሪ ሶሉሽን አካውንት ብቻ ነው፡፡ ባንካችን እነዚህን ፕሮዳክቶችን (አገልግሎቶችን) አዘጋጅቶ ለህብረተሰቡ ሲያቀርብ የራሱ የሆነ ዓለማና ግብ ኖሮት እንደመሆኑ መጠን አገልግሎቶቹን ተደራሽ ለማድረግ ባለፈባቸው ምዕራፎች ሁሉ አስፈላጊውን ገንዘብ፣ የሰው ጉልበትና ጊዜ አፍስቦታል፡፡ በመሆኑም በስራ ላይ የተስተዋሉ ክፍተቶችን በተለይም ከሽያጭ ጋር ተያይዞ የሚስተዋለውን የግንዛቤ ችግር በስልጠናዎች በመፍታትና አገልግሎቶቻችንን በስፋት በማስተዋወቅ ከዚህ የተሻለ ውጤት ማምጣት ይቻላል፡፡ ይህ በተፈለገው መልኩ እንዲሳካም ሁሉም ባለድርሻ አካላት የሚጠበቅባቸውን ድረሻ መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡

# አዋሽ ባንክ የካናዳ ክርስቲያን ህፃናት ፈንድ ከተሰኘ ግብረ ሰናይ ድርጅት ጋር በመተባበር የመማሪያ ክፍሎችን አስገነባ



በአዋሽ ባንክ የፋይናንስ ድጋፍ የተገነቡ የመማሪያ ክፍሎች በከፊል

አዋሽ ባንክ የካናዳ ክርስቲያን ህፃናት ፈንድ ከተሰኘ ግብረ ሰናይ ድርጅት ጋር በመተባበር በአዳማ ከተማ ከኢትዮጵያ ሱማሌ ክልል ለተፈናቀሉ ህፃናት የተሟላ የመጠጥ ውሃና ዘመናዊ መጸዳጃ ቤቶች እንዲሁም የህፃናት መጫወቻዎች ያሏቸው የመማሪያ ክፍሎችን አስገነባ፡፡

የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነቱን በመወጣት የሚታወቀው አዋሽ ባንክ ባለፈው ዓመት 25ኛ ዓመት የምስረታ በዓሉን ባከበረበት ወቅት ለተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች በሚሊዮኖች የሚቆጠር የገንዘብ ድጋፍ ማድረጉ ይታወሳል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ የብር አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ የገንዘብ ድጋፍ ያገኘው የካናዳ የክርስቲያን ህፃናት ፈንድ የተሰኘ ዓለም አቀፍ ግብረ ሰናይ ድርጅት ነው፡፡

ግብረ ሰናይ ድርጅቱ ከባንኩ ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ ከኢትዮጵያ ሱማሌ ክልል ለተፈናቀሉ ህፃናት መማሪያ የሚውሉ የመማሪያ ክፍሎችን ከዘመናዊ መፀዳጃ ቤቶች፣ ከህፃናት መጫወቻዎችና ከመጠጥ ውሃ ጋር በመገንባት ለህብረተሰቡ ያስረከበ ሲሆን ብሎኩንም በአዋሽ ባንክ ስም ሰይሟል፡፡ ትምህርት ቤቱም የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፣ የአዋሽ ባንክ የሥራ ኃላፊዎች እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት በይፋ ተመርቆ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል።

አዋሽ ባንክ በኮርፖሬት ማህበራዊ ሃላፊነት መርሀ-ግብሩ ውስጥ ከሰብዓዊ ዕርዳታዎች ጎን ለጎን ለማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ግንባታና ለአካባቢ ጥበቃ ሥራዎች ልዩ ትኩረት በመስጠት ይታወቃል፡፡

# አዋሽ ባንክ ከኢትዮጵያ የወንጌል አማኞች አቢያተ ክርስቲያናት ካውንስል ጋር የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረመ




*የመግባቢያ ሰነዱ የፊርማ ሥነ-ሥርዓት በከፊል*

አዋሽ ባንክ ከኢትዮጵያ የወንጌል አማኞች አቢያተ ክርስቲያናት ካውንስል ጋር አብሮ መስራት የሚያስችለውን የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረመ።

የመግባቢያ ስምምነቱን የፈረሙት የአዋሽ ባንክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ፀሀይ ሽፈራው እና የኢትዮጵያ የወንጌል አማኞች አቢያተ ክርስቲያናት ካውንስል ፕሬዝዳንት እያሱ ኤልያስ (ዶ/ር) ሲሆኑ በስምምነቱ ላይ ለእምነት ተቋማት ልዩ ትኩረት በመስጠት በርካታ የፋይናንስና ህብረተሰቡን ተጠቃሚ በሚያደርጉ እንዲሁም በተመረጡ የልማት ዘርፎች ዙሪያ በትብብር ለመስራት የሚያስችል መሆኑን የሁለቱ ተቋማት ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

አዋሽ ባንክ የመንግስትን አቅጣጫ በመከተል ከበርካታ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ጋር በትብብር ለመስራት የሚያስችለውን ስምምነቶች በማድረግ ላይ ሲሆን በዚህም በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ እየሆኑ ይገኛሉ። የኢትዮጵያ የወንጌል አማኞች አቢያተ ክርስቲያናት ካውንስል በስሩ ከሰላሳ ሚሊዮን በላይ አባላትን ይዞ እንዲሁም ከሰላሳ አምስት ሺህ በላይ ቤተ-እምነቶችን በማቀፍ ከተመሰረተ አንድ ዓመት ያስቆጠረ ቢሆንም የጎልማሳ ራዕይን ሰንቆና ሀገራዊ ፋይዳውን በማሳደግ እንዲሁም አፍሪካንና ዓለም ዓቀፍ ገጽታን በመገንባት ከመንቀሳቀሱም ባሻገር ህብረተሰቡን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ሰፊ የልማት ሥራዎችና የአካባቢ ጥበቃ ላይ በመስራት ላይ የሚገኝ የእምነት ተቋማት ካውንስል ነው፡፡

ካውንስሉ በሚሰራቸው የህብረተሰብ ልማት ስራዎች ከአዋሽ ባንክ ጋር በትብብር ለመስራት የተስማማ ሲሆን አዋሽ ባንክም በስምምነቱ መሰረት ለሀይማኖት ተቋማት ያዘጋጃቸውን የተለያዩ ፓኬጆችን ያካተተ የፋይናንስ አገልግሎት ማለትም ሃይማኖታዊ ፕሪሚየም የቁጠባ ሂሳብ፣ የደመወዝና ፕሮቪደንት ፈንድ አስተዳደር፣ የተለያዩ የግንባታ ብድሮች፣ገንዘብ የማሰባሰብ አገልግሎቶች (Cash Collection Services)፣ለሃይማኖት ተቋማት ተቀጣሪዎች ብድር ከማመቻቸት ጎን ለጎን ካውንስሉ ለተለያዩ የኢንቨስትመንት ስራዎች የብድር አገልግሎት ሲፈልግና የባንኩ የብድር ፖሊሲ ላይ የተቀመጡ መስፈርቶችን አሟልቶ ሲገኝ የብድር አገልግሎቱን ለማቅረብ በፈረመው ስምምነት አረጋግጧል፡፡

## አዋሽ ባንክ የአርሶ አደሮችን የቁጠባ ባህል በማሳደግ ላይ እየሰራ ነው

አርሶ አደሮች ገንዘባቸውን በባንክ የመቆጠብና ከግብርና ወደ ሌላ ኢንቨስትመንት ለሚያደርጉት ሽግግር ከባንኮች ጋር የመስራት ልምድ እንዲኖራቸው አዋሽ ባንክ ከአርሶ አደሮች ጋር በቅርበት እንደሚሰራ አዋሽ ባንክ ዋና ስራ አስፈፃሚ አስታወቁ፡፡

የአዋሽ ባንክ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ፀሐይ ሽፈራው ይህንን ያሉት የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የ2012/13 የምርት ዘመን የክልሉን ግንባር ቀደም አርሶ አደሮችን ለማበረታታትና ዕውቅና ለመስጠት በአዳማ ከተማ ባዘጋጀው ፕሮግራም ላይ በመገኘት ከአዋሽ ባንክ ጋር አብሮ እየሰሩና በባንኩ እየቆጠቡ ያሉ ግንባር ቀደም አርሶ አደሮችን ለማበረታታት እና በሌሎች አርሶ አደሮች ዘንድም መነሳሳትን ለመፍጠር ከ100 ሺ ብር እስከ 50 ሺ ብር ሽልማት ባበረከቱበት ወቅት ነው፡፡

የሽልማቱ ዋና ዓላማም የኢኮኖሚ ዕድገት መሰረት የሆነውን የቁጠባ ባህል ለማበረታታት እና አርሶ አደሮች ከባንኮች የመስራት ልምድ እንዲያደብሩ ታሳቢ በማድረግ ነው ያሉት አቶ ፀሐይ፣ አርሶ አደሮች ከግብርና ወደ ሌላው የኢንቨስትመንት ዘርፍ ለሚያደርጉት ሽግግርም አዋሽ ባንክ አብሯቸው ለመስራት ዝግጁ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ምቹ መሆኑንም ገልፀዋል፡፡

## አዋሽ ባንክ ባመቻቸው ብድር የዳንግላ ከተማ ዙሪያ አርሶ አደሮች ተጠቃሚ ሆኑ

አዋሽ ባንክ ከኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ (ATA) ፕሮጀክቶች መካከል አንዱ ለሆነው የግብርና ግብዓት አቅርቦት እና አገልግሎት ማዕከላት 'Agricultural One Stop Shop' ባለቤቶች ባመቻቸው የብድር አገልግሎት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለዳንግላ ከተማ ዙሪያ አርሶ አደሮች ትራክተሮች ተገዙ፡፡ የዳንግላ ዙሪያ አርሶ አደሮችም ትራክተሮቹን ተረከበዋል፡፡

ትራክተሮቹ የተገዙት አስተማማኝ እና ጥራት ያላቸው የግብርና ግብዓቶችን እና አገልግሎቶችን በተገቢው ጊዜ እና ተመጣጣኝ ዋጋ ለአርሶ አደሩ በአቅራቢያው በሚገኙ ወረዳዎች በሚቋቋሙ ሱቆች ማቅረብን ዓላማ ላደረገው የኤጀንሲው የአንድ መስኮት የግብርና ግብዓቶች አቅርቦት እና አገልግሎት ማዕከላት 'Agricultural One Stop Shop' አዋሽ ባንክ የብድር አገልግሎት ለመስጠት ከኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ (ATA) ጋር በተፈራረመው የመግባቢያ ሰነድ መሠረት በሰጠው ብድር ነው፡፡

አዋሽ ባንክ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎችን ማዕከል ያደረጉ የተለያዩ አገልግሎቶችንና ፕሮዳክቶችን በማቅረብ ሁሉን አቀፍ ዕድገት እንዲረጋገጥ ኃላፊነቱን መወጣቱን አጠናክሮ ይቀጥላል፡፡



# አዋሽ ባንክ ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት ጋር በመተባበር በመጋዘን ደረሰኝ መያዣነት የብድር አገልግሎት መስጠት ጀመረ




ከኢትየጵያ ምርት ገበያ ግብይት የተወሰደ

የመጋዘን ደረሰኝ ብድር አንድ አምራች ወይም ተገበያይ ምርቱን ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ መጋዘን በማስገባትና የመጋዘን ደረሰኙን (WR) እንደ ማስያዣ በመጠቀም ከምርት ገበያው ጋር በጣምራ ከሚሰሩ ባንኮች የብድር አገልግሎት የሚያገኝበት አሰራር ነው፡፡

በአገልግሎቱ መሰረት ተበዳሪው አርሶ አደር፣ የህብረት ስራ ማህበራት፣ ዩኒየኖች እና አቅራቢዎች ወደ መጋዘን ላስገቡት ምርት ከተሰጣቸው ደረሰኝ ውጭ ሌላ ንብረት ለመያዣነት ሳያስፈልጋቸው ከባንክ የአጭር ጊዜ የብድር አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ፡፡

አዋሽ ባንክም ከኢትዮጵያ የምርት ገበያ ድርጅት ጋር በመተባበር ለድርጅቱ ደንበኞች የአጭር ጊዜ ብድር አገልግሎት አቅርቧል፡፡ ባንኩ ይህንን የብድር አገልግሎት የሚሰጠው በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት እንዲገበያዩና በድርጅቱ መጋዘኖች እንዲከማቹ ለተፈቀደ የግብርና ግብዓቶች ብቻ ሲሆን የብድር አገልግሎቱን ለማግኘት አምራቾቹ ባንኩ በብድር ፖሊሲው ያስቀመጣቸውን መስፈርቶች አሟልተው መገኘት አለባቸው፡፡

# አዋሽ ባንክ ለገንዘብ ቁጠባና ብድር ማህበራት አማራጭ የፋይናንስ አገልግሎቶችን አቀረበ

አዋሽ ባንክ ለውድ ደንበኞቹ አስተማማኝ የፋይናንስ አገልግሎት ከመስጠቱ ባሻገር ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ፍላጎታቸውን መሰረት ያደረጉ አገልግሎቶችን ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ከዚህ አኳያ በፋይናንስ አገልግሎቱ ተደራሽ የሚሆኑት በየደረጃው ለሚገኙና በተለያዩ ማህበራት ውስጥ ማለትም በዕድሮች፣ ዕቁቦች፣ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ማህበራት እንዲሁም የሙያ ማህበራትና ሌሎችም ውስጥ ተደራጅተው የሚገኙትን የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ለማድረግ ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡

አዋሽ ባንክ ከላይ በተዘረዘሩት አደረጃጀቶች ውስጥ ለሚካተቱ ማህበራት ካዘጋጃቸው አማራጭ የፋይናንስ አገልግሎቶች ውስጥ በዋናነት የብድር አገልግሎቶች፣ የተቀማጭ ገንዘብ አገልግሎት (ተንቀሳቃሽ ሂሳብ፣ በተወሰነ የጊዜ ገደብ የሚቀመጥ ተቀማጭ፣ ልዩ የቁጠባ አገልግሎቶች ፣ የፔሮል ወይም ደመወዝ አስተዳደር አገልግሎት፣ የፕሮቪደንት ፈንድ ሂሳብ አስተዳደር አገልግሎት፣ ተቀማጭ ገንዘብ ለመሰብሰብና ገንዘብ ለመክፈል የቤት ለቤት አገልግሎት፣ የዲጂታል ቻናሎች አገልገሎት፣ የባንክ ዋስትና አገልግሎት እንዲሁም የስልጠናና የማማከር አገልገሎቶች በዋነኝነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ተቋማቱ የባንክ ብድር ለማግኘት ማሟላት ከሚጠበቅባቸው መስፈርቶች ውስጥ በዋናነት በህጋዊ የመንግስት አካል ተመዝግቦና ህጋዊ መስፈርት አሟልቶ ዕውቅና በማግኘት፣ የታደሰ ህጋዊ ፈቃድ በማሟላት፣በባንክ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችል በቂ የአባላት መጠን፣ በየጊዜው የሚሰበሰብ ገቢና የካፒታል መጠን ይዞ በመገኘት፣ለውስጥ የፋይናንስ አስተዳደር ምቹና ተገቢነት ያለው የሂሳብ አሰራር ተግባራዊ በማድረግ፣ ተንቀሳቃሽ ወይም የቁጠባ ሂሳብ ኖሯቸው በዚህ የባንክ ሂሳብ በየጊዜው የሚሰበሰበውን ቋሚ ገቢና ሌሎች አከፋፈሎችንም ለማድረግ ከስምምነት ሲደርሱ ፣ባንኩ ሲፈልግ ተቀማጭ ገንዘብ በመሰብሰብ፣ ክፍያዎችን ለመፈፀምና የአገር ውስጥ የገንዘብ ዝውውሮችን ለማከናወን የወኪልነት ሚና በመጫወት ፣ የአባላቱንና የደንበኞቹን የቁጠባ ባህል ለማበረታታት የባንኩን ሙዳይ የቁጠባ ሳጥኖችን በማሰራጨት፣ በየጊዜው የሚሰበስቡትን ቋሚ መዋጮ ወይም ቁጠባቸውን በባንኩ በማስቀመጥ እንዲሁም የባንኩን የብድር ፖሊሲ መስፈርቶችን አሟልቶ በመገኘት የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የአገልግሎት አሰጣጡን ከግዜ ወደ ግዜ በማዘመንና ለደንበኞች በይበልጥ ተደራሽ በመሆን ላይ የሚገኘው አዋሽ ባንክ ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ፍላጎታቸውን ማዕከል ያደረጉ አገልግሎቶችን ለመስጠት ተግቶ ይሰራል።

Easy access, Many Solutions ...




አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like the River

# DIGITAL BANKING TECHNOLOGY

Online banking means accessing banking features and services via your bank's website from your computer. You may log into your account to check your balance or pay your electricity bill. You can access additional banking features, such as applying for a loan or credit card, at many banks via your online banking portal.

Online banking lets you sit down at your computer and tackle many of your personal finance needs without ever having to leave your home, something for which the family pet is likely most grateful.

Mobile banking means using an app to access many of those same banking features via mobile devices such as smart phones or tablets. These apps are proprietary, issued by the bank where you hold your account, and usually use the same login information as your Online banking portal.

Designed for people on the go, mobile banking apps tend to include the most used banking features, such as mobile check deposit, funds transfers and bill payment. They also often have convenient features like peer-to-peer payments through systems like Zelle. Banks also may use their mobile apps to send customers banking alerts such as fraud detection and low balance notifications.

Online banking in the U.S. has its roots back in the 1990s. In October 1994, Stanford Federal Credit Union was the first institution to let its customers access banking



functions via the new World Wide Web. By the time the 21st century rolled around, it's estimated that 80% of U.S. banks offered their customers the ability to bank Online.

As mobile devices gained popularity and adoption, banks were encouraged to put their services at their customers' fingertips and create their own mobile banking apps. As of its most recent biennial, "How America Banks," the FDIC reported that 34% of Americans used mobile banking as their primary way of accessing their accounts in 2019.

Together, online and mobile banking create the digital banking umbrella, giving people access to banking wherever they maybe or, in some cases, wherever they're graced with secure Wi-Fi and strong cell signal.

## WHAT ARE THE BENEFITS OF DIGITAL BANKING?

Digital banking offers a number of benefits for both consumers and business owners. Here are several:

### Access

With both desktop and mobile access to your bank accounts available, digital banking means you're not beholden to bank hours to manage your finances.

### Better rates and lower fees

With online banks driving fees down, consumers have choices beyond their local brick-and-mortar financial institutions. It's easy to compare rates and fee structures to find the best bank for your needs.

### Equity

Upstart online banks level the banking access playing field by reaching unbanked and underbanked communities that rely heavily on mobile phones but may not have access to physical bank branches.

Source - https://www.forbes.com/advisor/banking/what-is-digital-banking

# FIVE FINANCIAL GOALS YOU SHOULD HAVE FOR 2021

## 1. TO HAVE CONTROL OF MY MONTHLY BUDGET

If you are not used to keeping track of your money, this is a good time to start. It is very important that you know how much money you are spending and on what, but it is even more important to know how much money goes into your pocket.

If you are not one of those who is used to recording each expense and income in a notebook (because you always forget it), use an app because we are all glued to the cell phone and what better way to use it to better control our money.

## 2. REDUCE ANT EXPENSES

The worst sabotage you can do to your finances is having ant expenses and not being aware of them. We are talking about coffee in the morning, potato chips in the afternoon and everything that disappears in a moment and contributes to empty your wallet.

## 3. DO NOT MAKE EMOTIONAL PURCHASES

Even if it is not a season of sales or sales, always take at least a minute to think if you really need what you are going to buy, especially when you go to the supermarket. Always try to carry a list of what you should buy and whenever you see something that is not included, remember to ask yourself: do I want it or do I need it?

## 4. BETTER MANAGE MY MONEY

In order to better manage your money, it is necessary that you first identify what you are doing wrong or what are the points to improve so that you can boost your results.

## 5. PAY MY DEBTS ON TIME

Debts are one of the most common problems that people deal with and it is not bad to have debts, what is bad is that they get out of control and then you do not know what to do. Ideally, if you have debts, you liquidate them immediately, but if you do not have capital to cover the total amount, advance payments, so that you reduce them as much as you can and they stop being a concern for you.

Source https://www.entrepreneur.com/article

# PHOTO REEL















**Pictorial Memory of Semi-Annual Management Meeting at Elilly Hotel**

# ኮሮና ቫይረስን በጋራ እንከላከል!!

## የበሽታው ምልክቶች | Symptoms



ትኩሳት
**High Fever**



የትንፋሽ ማጠር
**Trouble Breathing**



ሳል
**Cough**

## የሚደረጉ ጥንቃቄዎች | Prevention



አለመጨባበጥ
do not shake hands




ባልታጠበ እጅ ፊትዎን አለመንካት
Avoid touching Eyes, Nose & Mouth



አፍን መሸፈን
Use face mask



እጅ በሳሙና መታጠብ
Wash your hands with soap & water



አካላዊ ርቀትን በ2 ሜትር መጠበቅ
Keep 2m distance from others

# Proverbs & Quotes

All our dreams can come true  if we have the courage to pursue them

Walt Disney

Always keep your eyes open  Keep watching  Because whatever you see can inspire you

Grace Coddington

What you get by achieving your goals is not as important as what you become by achieving your goals

Henry David Thoreau

If the plan doesn t work  change the plan  but never the goal

Author Unknown

Champions keep playing until they get it right

Billie Jean King




# የተሟላ ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት

12638 8980
www.awashbank.com
contactcenter@awashbank.com

አዋሽ ባንክ
AwashBank

ikhlas
Nurturing Like the River